# የስርዓት መውደቂያው ሲቃረብ መንግሥታዊ ሽብር ይፋፋማል!

ግንቦት 27ቀን 2015 ዓም (04-06-2023)

እያደር እዬጨመረ የመጣው የሥርዓቱ በደልና ክፋት የአሸናፊነት ወይም የበላይነትን የሚያሳይና የሚያረጋግጥ ሳይሆን የመውደቂያው ምልክቶች ናቸው።የተረጋጋና ሕዝቡን ከኋላው ያሰለፈ ስርዓት በሚጠቅሙና ሕዝቡን በሚያረኩና በሚያስደስቱ ተግባራት ላይ ይሰማራል እንጂ ሕዝቡን በማሸበር፣ በማሳደድ፣በመግደልና በማፈናቀል ላይ አይሰማራም።አገርን በጠንካራ ዋልታ ላይ የገነባ መንግሥት ደሞዝ መክፈል አቅቶት ያገር ሃብትና ቅርስ ለመሸጥ ገበያ አይወጣም።ሕዝብን በማስጨነቅ ግብርና ቅጣት አይጥልም ፣አይዘርፍም።የሕዝብ ድጋፍ ያለው መንግሥት ሕዝቡን አስገድዶ ደግፉኝ ሰልፍ ውጡልኝ አይልም።ባለፈው ሰሞን ያዬነው ይህንን ሁኔታ ነው።በመሬት ላይ ያለው ሃቅ ገዥው ቡድንና ደጋፊዎቹ እንደሚሉን ሳይሆን የተገላቢጦሽ ነው።የሚሉትና የሚታዬው ሆድና ጀርባ ነው።

በኢትዮጵያ ምድር ላይ ላለፉት 32 ዓመታት የሰፈነው ስርዓት አገር ጠል የሆነ ስርዓት ነው።በዚህ ላይ የሚግደረደር ካለ የሥርዓቱ ደጋፊና አካል ወይም በቀውስ ላተርፍ እችላለሁ ብሎ የሚያስብ እራስ ወዳድ ብቻ ነው።አገር ማፍረስ ማለት መሬቱን መናድ ማለት ሳይሆን በመሬቱ ላይ የሚኖረውን ሕዝብ እርስ በርሱ እያዋጉ አንድነቱን አናግቶ፣ ሰላም አጥቶ ፣ሁሉም በዬፊናው በጠላትነት ተሰልፎ እንዲተላለቅ ፣የሚግባባበትን ቋንቋ ፣የሚጋራውን የእምነትና የባህል እሴቶቹን ማዳከምና ማፍረስ፣ ታሪኩን በመጥፎ ትርክት ለውጦ ባለፈው ታሪኩ እንዲያፍርና ማንነቱን እንዲጠላ ማድረግ ማለት ነው።ለብቻው በእምነቱ፣ በቋንቋና በጎሳ ማንነቱ ምድራዊ ገነት የሚፈጥር በማስመሰል እራስ ወዳድነትን በሰዎች ህሊና ቀርጾ ተባባሪና መሳሪያ ማድረግ ማለት ነው።ጎሰኝነት ሌላውን የሰው ልጅ ጠልቶ እንደሰው እኖራለሁ ብሎ የማሰብ የአይምሮ እክል ወይም የበታችነት የሚፈጥረው የማይድን በሽታ ነው።ለዚያም ነው ዘረኝነት ወይም ጎሰኝነት ካንሰር ነው የሚባለው።ታዲያ ይህንን ካንሰር በሽታ ቆርጠው ይገላገሉታል እንጂ በመታገስ ተሸክመውት አይኖሩም።

*አንድን ስርዓት መንግሥታዊ ተፈጥሮ እንዳለው ለማወቅ በቅድሚያ የመንግሥትነትን ባህሪና ተፈጥሮ መረዳቱ ተገቢ ነው።*

*መንግሥት ማለት መርህ ያለው፣ በሕዝብ ፍላጎት ተመርጦ ሥልጣን ላይ የሚቀመጥ፣የሕዝብ ወኪል፣ አላፊነቱንና አደራውን የሚወጣ ሕግ አክባሪና አስከባሪ፣ እንዲሁም ግንባር ቀደም ምሳሌ የሚሆን ማለት ነው።ከዚያም በተረፈ የአገሩን ዳር ድንበር የማያስደፍር ፣ልዑላዊነትን የሚያረጋግጥ፣የሕዝቡን ደህንነትና ሰላማዊ ኑሮ የሚያስከብር ፣ግጭትና ጦርነትን አሶግዶ አንድነቱንና ግንኙነቱን የሚያጠናክር፣ ታሪክና እሴቶችን የሚንከባከብ፣ባሉት ላይ ሌሎች መልካም አገራዊ እሴቶችን የሚጨምር፣መጥፎ ባህልን የሚያሶግድ፣ጥሩ ባሕሎችን የሚያሳድግ፣ከኋላ ቀር አስተሳሰብ የሚያወጣ፣አገርን ለእድገት የሚያበቃ አስተሳሰብንና የፈጠራ ሥራዎችን የሚያበረታታ፣አገርና ሕዝብን ከቀረው የዓለም ማህበረሰብ ጋር በኑሮ ደረጃም ሆነ በአስተሳሰብ የሚያቀራርብ፣በራሱ የሚተማመን ሕዝብ እንዲኖር የሚያደርግ ፣ ወንጀልና ወንጀለኞችን የሚቀጣና ለዘለቄታው የሚያጠፋ ፍትህን በተግባር የሚተረጉም፣ላለበት ትውልድ ብቻም ሳይሆን ለተተኪ ትውልድ የሚጨነቅና አቅጣጫ የሚነድፍ ---ወዘተ አካል ማለት ነው።*

እነዚህን እንደመለኪያ አድርገን ላለፉት 50 ዓመታት፣በተለይም ላለፉት 32 ዓመታት ይባስ ብሎም ላለፉት 5 ዓመታት በኢትዮጵያ አገራችን የሰፈነውን ስርዓት ስንመረምር የመንግሥትነት ጸባይ

የሌላቸው አምባ ገነኖች፣ሌቦችና ዘራፊዎችም ብቻ ሳይሆኑ አገር ለማጥፋትና ለመበታተን ዓልመው የሚሰሩ ወንበዴዎች መሆናቸውን እናረጋግጣለን። ገና ሲጀምሩ የጎሳ ፖለቲካን መመሪያ ያደረጉት ለጎሳ ተጨንቀውና ተጠበው፣ካለበት የመከራ ኑሮ ለማውጣት ሳይሆን የነበረውን አጥቶ ከባሰ ችግርና ቀውስ ውስጥ እንዲገባ፣የትልቅ አገር ባለቤት ከመሆን ይልቅ የሰፈር እስረኛ ሆኖ በሚኖረው ጠባብ ዕድልና የተፈጥሮ ሃብት እርስ በራሱ እዬተጋደለ ሰላም ናፍቆት እንዲኖር ፣በመጨረሻውም ለውጭ ወራሪዎች የተመቸ እንዲሆን የማድረግ ተልእኮ አንግበው የተነሱ አገር ብቻም ሳይሆን ሰው ጠሌ የሆኑ አረመኔዎች ናቸው።መንግሥት ቢሆኑ ኖሮ ወይም የመንግሥትነት ተፈጥሮ ቢኖራቸው ኖሮ አገርን እንደ አገር ሕዝቡንም እንደ አንድ አገር ዜጋ ባዩት ነበር።አሁን ለሚታዬው ቀውስ፣የእርስ በርስ ግጭት፣ ድህነት፣መፈናቀል ባልዳረጉት ነበር።

የአንድ አገር መንግሥት የአገሩን ታሪክና ተውፊቶች ካላከበረና ፣ የአገርን ዳር ድንበርና ልዑላዊነት ካላስከበረ ፣የሕዝቡን ኑሮ ካላሻሻለ፣በድህነት አሮንቃ ውስጥ እንዲማቅቅ ካደረገ የመንግሥትነት ግርማ ሞገስ አይኖረውም።ያኑርህ ሳይሆን ይንቀልህ ተብሎ የሚረገም የታሪክ ቁሻሻ ይሆናል።ነውም። ለዚያም ነው ከደርግ አገዛዝ ጀምሮ በወያኔና አሁን በሥልጣን ላይ  ባለው የኦነግ ኦሮሙማ ቡድን ላይ የሕዝቡ ተቃውሞና ትግል በዬቦታው የተቀጣጠለው።ትግሉ ባዬለ ቁጥር የመውደቂያ ጊዜው መቃረቡን በወደቁት የዘውዳዊ፣የደርግና የወያኔ ስርአቶች ተረድተናል።መውደቂያ ሲቃረብ የሚወሰደውም የጭካኔ እርምጃ እንደዚያው በመጠንም በደረጃም እንደሚጨምር ታዝበናል።፣ይባስ ብሎ የአገር ሃብት የሚመዘብርና ሕዝቡንም በተለያዬ ምክንያት አስገድዶ የሚዘርፍ ከሆነ የመውደቂያውን ጥርጊያ መንገድ እዬቀዬሰ ለመሆኑ ከሌሎች አገሮች  አምባገነኖች ውድቀት ጋር ማገናዘብ ይበቃል።ሕዝብ ጠልቶት በሥልጣን ላይ የቆዬ ስርዓት የለም፣አይኖርምም።የጊዜ ጉዳይ እንጂ ከመፈረካከስ የሚድንበት ዕድሉ ጠባብ ነው።እርግጥ ነው ሲፈራገጥ ጉዳት ሊያመጣ ይችል ይሆናል።በተለይም ሕዝብ በአንድነት ቆሞ የጋራ ጠላቴ ነው ብሎ ካላሰበ ለጊዜውም ቢሆን ለወንጀለኞች ጊዜያዊ ድል ሊያመጣላቸው ይችል ይሆናል እንጂ ዘለዓለማዊ አይሆኑም።ዕድሜያቸውን የሚያሳጥረው የሕዝቡ አንድነትና የትግሉ ጥንካሬ ነው።

የሕዝቡን አንድነትና የትግል ጥንካሬ ስንፈትሸው እንደመከራው ክብደት፣እንደ ሥርዓቱ ጭቆናና ጸባይ አይደለም።በትግል ሜዳ ተሰልፎ መስዋእት የሚከፍለው የህብረተሰብ ክፍል በጣም ጥቂቱ ነው።ለዚያ ዋናው ምክንያት የንቃተ ሕሊና ማነስ ሲሆን በጥቅመኞች የማምታታት ሴራ መተብተብ ሌላው ምክንያት ነው።በትግሉ ሜዳ የሚፋለመው የመከራው ሁሉ ገፈታ ቀማሽ የሆነው በአገር ወዳድነቱ የሚታወቀውና እንዲጠፋም የተፈረደበት የአማራው ማህበረሰብና የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ፣እንዲሁም የነባሩ የእስልምና እምነት ተከታይ የሆነው አገር ወዳድ ብቻ ነው።መታወቅ ያለበት የነዚህም ማህበረሰብ ተወላጅና የዬእምነቱ ተከታይ በሙሉ ለመብቱና ለአገሩ አንድነት ቆሟል ማለት አይደለም።እንደውም ለስርዓቱ አገልጋይና ተላላኪ ሆኖ የጥቃት መሳሪያ የሆነው ከነዚሁ ጉዳተኞች የወጣ ዜጋ ነው።ለጥቂት ጊዜያዊ ጥቅም ሲል የራሱን ወገን ለመከራ አሳልፎ የሚሰጠው፣የአገሩን መፈራረስ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚረዳው ከዚሁ ማህበረሰብና ከእምነቱ ተቋማት የወጣው አድር ባይ ነው።ብአዴን፣አብን፣ኢዜማና መሰሎቻቸው ፣ምሳሌዎች ናቸው።እነዚህ ጉደኞች በፖለቲካ ድርጅትነት የስርዓቱን እውቅና አግኝተው አጃቢ ከመሆንም በላይ የሹመት ተካፋዮች ናቸው።ሌሎቹ ከሃምሳ በላይ የሚሆኑት የፖለቲካ ድርጅት ነን ባዮች ተቃዋሚ ነን እያሉ  የሕዝቡን ስቃይና የአገሪቱን የመፈራረስ አደጋ እያዩ ድምጻቸውን ለማሰማት አልደፈሩም፣ሕዝቡ የሚያደርገውን የሞት የሽረት ትግል ሲሆን መምራት አለያም ማገዝ ሲኖርባቸው ድምጻቸውን አጥፍተው ቁጭ ብለዋል፣ከመንግሥት የሚወረወርላቸውን ድጎማ ግን እምቢ፣ከደሃው ሕዝብ ያላግባብ የሚሰበሰብ ሃብት ነው አላሉም፤የሚጨቃጨቁት አነሰን ይጨመርልን በማለት ነው።

የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አያሌ በደል ሲደርስባት ፣ከ700 ዓመት በላይ የኖሩ ገዳማት ሲፈራርሱ፣መነኮሳት በጥይት ሲደበደቡ፣ምእመናን ሕጻን ሽማግሌ ሳይባል ሲረሸኑ የእምነቱ ተከታይ ቀርቶ የቤተክህነት አባቶች ድምጻቸውን አላሰሙም።በጣም የሚገርመው በአገር ውስጥ ታሪክ ያላቸው የዘመናት ገዳማት በአገር ጠሉ የኦነግ ወራሪ ሲቃጠሉ በዝምታ የተቀመጡት ጳጳሳት በውጭ አገር በአሜሪካ፣በአውሮፓና በአረብ አገር ገዳም ተሰራ ብለው ለመመረቅ ሲራኮቱ ማዬቱ ያስተዛዝባል።ይባስ ብሎም በዚሁ ሰሞን ፓትሪያርኩ አቡነ ማትያስ ወደ አረብ ኢሚራት መሄዳቸው የሰውዬውን ምንነት ያጋልጣል።ምእመናን በሚጨፈጨፉበት ጊዜ ካገር መውጣታቸው መንጋውን ለአውሬ ጥሎ እንደመሸሽ ይቆጠራል። ታዲያ ተራው ምእመን ማንን አይቶ ለትግል ይሰለፍ? የትኛውን ጳጳስ ተከትሎ ለመብቱና ለእምነቱ ይቁም?

በሙስሊሙም በኩል እንዲሁ ነው።በአዲስ አበባ ከተማ በመርካቶ አንዋር መስጊድ ውስጥ ለጁማአ ሶላት የወጡ ወገኖቹ መስጊዳቸው ተሰብሮ በጥይት ሲደበደቡና ሁለት ተገለው ብዙዎች ሲቆሰሉ የወሎ ፣ የትግራይ፣የአሩሲ ፣የጎጃም፣የጎንደር፣ የባሌ፣የወለጋ፣የከፋ፣ የአፋር፣የሶማሌ፣የሲዳማ --- ሙስሊም ከጎኑ አልቆመም።ይባስ ብሎ በአዲስ አበባ የሚኖረው ሙስሊም የአረመኔው ስርዓት የፖሊስ ሃይሎች ሰፈር ለሰፈር እዬዞሩ ወጣቱን ሲያድኑ ተመልካች ሆኗል።ወንጀለኛውን ስርዓት ይወገድ ብሎ ከመታገል ይልቅ ሕግ ይከበርልን እያሉ በመጠዬቅ ወንጀለኛውን ዳኛ አድርገው ይማጸኑታል። ኢማሙም የስርዓቱ ተሿሚ ስለሆኑ ግማሽ ልብ ናቸው።

በግንቦት 25 ቀን አርብ በተመሳሳይ ለሶላት የወጣው ሙስሊም ድምጻችን ይሰማ እያለ በሰላማዊ መንገድ ጥያቄ ሲያቀርብ በድጋሚ በስርዓቱ ሰርጎ ገቦች በተቀሰቀሰ ረብሻ ተመሳሳይ ከበባ ተደርጎበት በጥይት ተደብድቧል።ቁጥራቸው ያልታወቁ ንጹሃን ሞተዋል፤ብዙዎችም ቆስለዋል።በመርካቶ ዙሪያ በተፈጠረው የስርዓቱ ታጣቂ በፈጠረው ቀውስ ከባቢው በባሩድ ሲታጠን ውሏል።የንግድ ተቋማት በሙሉ ተዘግተዋል። የስርዓቱ ጭፍጨፋ በአዲስ አበባ ብቻ ተወስኖ አልቀረም።በሻሸመኔ፤ በጅማ፣ በሐረር እንዲሁ በሕዝበ ሙስሊሙ ላይ ተመሳሳይ እርምጃ ተወስዶ ብዙዎች ተገለዋል፣ቆስለዋል። በሌሎቹም አካባቢዎች የመቀጣጠሉ ሂደት ታይቷል።ጭራሽ የሚበርድ አይሆንም።

የኦርቶዶክስና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በጋራ ቆመው የጋራ ጠላታቸው በሆነው የኦነግ ስርዓት ላይ መነሳት ያለባቸው ጊዜው አሁን ነው።መከፋፈሉ የጠላታቸውን ዕድሜና ጉልበት ያጠናክረዋል እንጂ መከራቸውን አያሶግደውም።የጎሳና የእምነት አጥር ሊከልላቸው አይገባም።በሰውነታቸውና በኢትዮጵያዊነታቸው ለመብታቸው አንድ ላይ መሰለፍ ይኖርባቸዋል።የአንዱ ጉዳት ሌላውን ሊሰማው ይገባል።በዚህ ስርዓት ያልተጎዳ የህብረተሰብ ክፍል የለም፤ሁሉም የደም እምባ እያለቀሰ ነው።የደላቸው በስልጣን ላይ የተቀመጡትና ቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ለጥቅም ያደሩ ሆድ አደሮች ብቻ ናቸው።

በአዲስ አበባ ከተማ ለዘመናት የኖሩ ዜጎች በማንነታቸው ምክንያት ቤታቸው ሲፈርስና ሲፈናቀሉ ሌላው የከተማው ነዋሪ ተመልካች ሆኗል፤ነገ የሱ ተራ እንደሚሆን አልተገነዘበውም።ቢገነዘበውም በፍርሃት ዱካክ ውስጥ ተቀምጦ ሞቱን ይጠብቃል።ይባስ ብሎ ድምጻቸውን የሚያሰሙትን ዝም እንዲሉ ይማጸናል።በዬቀኑ በመቶ የሚቆጠሩ የሕዝብ ልጆች ሲታፈኑ አላዬሁም አልሰማሁም ይላል። ጋዜጠኞች፣ምሑራን፣ለስርዓቱ ያላደሩ ነጋዴዎች በማንነታቸውና በአቋማቸው እዬታፈሱ እስር ቤት ሲወረወሩ ለምን ብሎ መጠዬቅ ሳይሆን ለችግር የተጋለጡትን ቤተሰቦቻቸውን ለማጽናናት አልደፈረም። ላለፉት 8 ወራት በእስር ቤት የሚማቅቀው የ83 ዓመቱ አንጋፋ ጋዜጠኛና የታሪክ ተመራማሪ፤ደፋር አገር ወዳድ፣ከአማራው በላይ ለአማራው የሚከራከረው የወላይታው ተወላጅ ታዲዎስ ታንቱ ህጻናት ልጆቹንና ባለቤቱን ተለይቶ አሁንም በእስር ቤት እዬተሰቃዬ ይገኛል።የቆመለት የአማራ ማህበረሰብ ተወላጅ የሆኑት የባእዴንና መሰሎቹ የስርዓቱ ጃንደረባዎች በዚህ አዛውንት ላይ

ሲፈርዱበት ሌላው በዝምታ ተባባሪ ሆኗል።ሌሎቹም አገር ወዳዶች እንዲሁ የመከራ ጽዋ እዬተጎነጩ ነው።ሕዝብ ማለት የሰዎች ስብስብ ወይም ጥርቅም ማለት ነው።ሰው ማለትም ከእንስሳት የተለዬ አስተዋይ አይምሮ ባለቤት ማለት ነው። ሕዝብ ተብሎ የሚጠራው ለአገሩና ለወገኑ የሚቆረቆር፣ክፉና ደጉን የሚለይ እንጂ እንደ አሸዋ መሬት አልብሶ፣እንደነቀዝ ለሆዱ የሚርመሰመስ ትል ማለት አይደለም።በአምባገነኖች መዳፍ እዬተረገጠ እንደ እንስሳ ግባ ውጣ የሚሉትም መንጋ አይደለም። ሰው ወይም የነቃ ሕዝብ ማለት ለአገሩና ለሰብአዊ ክብሩ ፣ለፍትህ የሚቆምና ዋጋ የሚከፍል ጀግናና ደፋር ፣የሃሳብና የእውቀት ልእልና ያለው፣ ከአገሩ አልፎ ለዓለም ደህንነት፣እድገትና ሰላም የሚተጋ፣ ለእንስሳትና ለእጽዋት ደህንነት የሚያስብ፣ ለሆዱ ብቻ ያላደረ ከአውሬ የተለዬ ፍጡር ማለት ነው።

አሁን በኢትዮጵያ ሁኔታዎች እዬተለወጡ መጥተዋል፣አገር አፍራሹ ጎሰኛ ቡድን የፈለገውን የሚያደርግበት ጊዜ የሚያልቅበት ይመስላል።በዬአቅጣጫው ሕዝባዊ ተቃውሞ እዬተቀጣጠለ መጥቷል። የአማራው ፋኖ ብቻውን በመፋለም የጀመረው ትግል ሌላው አማራ እዬተቀላቀለው መሄዱን የሚያሳዩ ምስሎችና መግለጫዎች እዬወጡ ነው።ይህ አበጀ የሚባል ሲሆን በቂ ነው አንልም። እንደ በደሉ ብዛት ሁሉም አማራና የአማራ ወዳጅ ወይም ለሰብአዊ መብት፤፣ፍትሕና ለአገር አንድነት የሚቆረቆር ሁሉ የትግሉ ተካፋይ ሊሆን ይገባዋል።አማራው ለእኩልነትና ለፍትሕ፣ለአገር አንድነት ብሎ እንጂ እራሱን በሌሎቹ ላይ ለመጫን የወያኔና የኦነጎች ተወዳዳሪ በመሆን አይደለም።ያንንማ ቢያስብ ኖሮ ገና ከጅምሩ ጠላቶቹ ከንዳቸው ሳይበረታ መስበር በቻለና በበላይነት በተቀመጠ ነበር። የአማራው ፍላጎት የሁሉም ዜጋ መብት ተከብሮ የሚኖሩባት የተሻለች ኢትዮጵያን መፍጠር ነው። ታሪኩም የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው።

አሁን የስርዓቱ የመከላከያ አባላትም እያፈነገጡ የሕዝቡን ትግል በመቀላቀል ላይ ናቸው።በዚህ የተደናገጠው የኦነግ ቡድን መከላከያውን በሙሉ የኦነግ አሽባሪ ቡድን ከላይ እስከ ታች ድረስ እንዲቆጣጠረው ማድረግና የሌላውን ጎሳ ተወላጆች መንጥሮ ማባረር ወይም በስውር መግደል ነው። የኢትዮጵያ መከላከያ ብለህ የምትጀጃል ያለህ ብቸኛ አማራጭ ከስህተትህ ታርመህ እውነተኛ ያገር መከላከያ እንዲፈጠር ሕዝባዊ ጦሩን መደገፍና መቀላቀል ብቻ ነው። በኦነግ በኩል የሚረጋገጥልህ መብትህ ሳይሆን ሞትህ ነው። በአሸባሪዎች እጅ ላለመሞት ብቸኛው ምርጫ እራስን ማዘጋጀትና በትግሉ ሜዳ መሰለፍ ነው።ትግል ሲባል ለጠመንጃ ትግል ጦር ሜዳ መዋል ብቻ ሳይሆን ብዙ የትግል መስኮች ስላሉ በነዚያ ውስጥ በሚችሉት መንገድ መሳተፍ ነው።የዲፕሎማሲ፣የኤኮኖሚ፣የፖለቲካ ፣ የማህበረሰብ መስኮች ሁሉ የትግሉ መስኮች ናቸው።በከተማ የሕዝብ እምቢባይነትን መቀስቀስ፣ የተቃውሞ ሰልፍና የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ፣የንግድና ያገልግሎት ተግባራትን መገደብ፣ስንቅና ትጥቅ ማዘጋጀት፣የቆሰለውን ማከም፣የታሰረውን መጠዬቅ---ወዘተ የአርበኝነት ሥራ ነው።

በአማራው ክልል ውስጥ የአነጋዊያን ወረራና ጭፍጨፋ፣በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ላይና በሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ የተከፈተው ዘመቻ ፣የገዳማት መቃጠል፣የመsgidoce መፍረስ ለሥርዓቱ መውደቅ መንደርደሪያ መሆናቸው በገሃድ እዬታዬ መጥቷል። የጎጃም አርሶ አደሩ በዘርና በማዳበሪያ ሰበብ አደባባይ ወጥቶ ተቃውሞ በማሰማት ላይ ነው።ይህ ሕዝባዊ ተቃውሞ በትናንሽ ጥቅሞች እንዳይደለልና እንዳይቆም የማድረግ ሥራ መሠራት አለበት።የኑሮ ውdn,ቱ ጣራ ነክቷል።ይህ ይሻላል የሚሉት ነገር የለም።

የጎሰኞቹ ቡድን በአንድ በኩል የጭካኔ እርምጃውን ፣በሌላ በኩል የእርቅና ድርድር በሚል ሰበብ ለማጭበርበር ስልት ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።ውጥረት ሲበዛበት ብልጽግና በሚለው ድንኳን ውስጥ የተጠቀጠቁት ወንጀለኞች ስብስባ ላይ መክረማቸውን ሰምተናል።ተሰብስበው ቀና መፍትሔ ይፈጥራሉ ተብሎ ባይጠበቅም በአገሪቱ ውስጥ ያለውን ችግር ለመደበቅ አልቻሉም።የችግሩ ምንጭ

ፋኖ እንጂ እነሱ ያሰፈኑት ስርዓት መሆኑን አላመኑም።ለዚያም ፋኖን ለማጥፋት ወስኖ ስብሰባውን አጠናቋል።የሚገርመው ነገር አገር ያለችበትን ገሃድ እውነታ በሚጻረር መልኩ እድገት፣ሰላምና የኤኮኖሚ እምርታ የታዬበት ወቅት ላይ ነን፣ከ7% በላይ የኤኮኖሚ እድገት መዝግበናል ሲል በራሱ ላይ ያላገጠ መግለጫውን አሰምቷል።ሕዝቡም ለማያውቅሽ ታጠኝ ብሎ የዓመቱ ቀልድ አድርጎ ወስዶታል።በሌላም በኩል ከፋኖ ጋር እንደራደር አንደራደር የሚል ውይይት መደረጉን ሰምተናል።ፋኖ ስርዓቱን ለማስገድ የተነሳ ሕዝባዊ ሃይል እንጂ ከወንጀለኞች ጋር ጎን ለጎን ተቀምጦ ይደራደራል የሚል ሃሳብ የለንም። ለዚህ አይነቱ ጥሪ ጀሮ እንደማይሰጠው እንተማመናለን። ከጠላት ጋር የሚደራደሩበት አንድም የጋራ ነጥብ የላቸውም።

አገር አጥፊው ሥርዓት በውጭ አገር ያለውን ተቃዋሚም ለማዳከም ስልት ቀይሶ በመንቀሳቀስ ላይ መሆኑን ታዝበናል።ለግል ጥቅማቸውና በጎሳ ትስስራቸው ለስርዓቱ ያደሩ ሆድ አደሮች በልዩ ልዩ መንገድ ማለትም እርዳታን በማስተባበር፣ዘፈንና የእስፖርት ፌስቲቫል በማዘጋጀት ለስርዓቱ የገንዘብ ተፋሰስ ለማድረግና ህብረተሰቡን ከትግል ለማራቅ ብሎም የፖለቲካ ሽፋን ለመስጠት በሚያስችለው ተግባር ላይ ተሰማርተዋል። ይህ በኤምባሲዎች አስተባባሪነት የሚካሄደው እንቅስቃሴ ከአገር ቤቱ የስርዓቱ ተላላኪዎች ጋር የተሳሰረ መሆኑ ተደርሶበታል።በአገር ቤት ያሉ ነጋዴዎች በዝግጅቱ ላይ ትርፍ ታገኛላችሁ በሚል ቅስቀሳ ገንዘብ እንዲያዋጡ የሚሯሯጡ ልማደኛ ሌቦች መሆናቸውም ተደርሶበታል።ይህንን የወንጀለኞች እንቅስቃሴ ማምከን አለያም አለመሳተፍ ከሁሉም አገር ወዳድ ይጠበቃል።

በሌላውም ዙሪያ ከሚታዩት ድክመቶች አንዱ ትግሉን ለመምራት ዓላማና ፕሮግራሙን ነድፎ የወጣ የፖለቲካ ድርጅት አለመኖሩ ነው።የሚደረገው ትግል አገርና ሕዝብን የማዳን ትግል እንደመሆኑ መጠን አገር ወዳዶችን ያሳተፈ፣የጋራ የፖለቲካ ፕሮግራምና አመራር ያለው ድርጅት መኖር ወሳኝ ነው። የአማራው ሕዝባዊ ግንባር ለአማራው ህልውና የተደራጀ እንደመሆኑ መጠን ፣አማራው ለአገር አንድነት ካለው ድርሻና አቋም አንጻር የጋራ አመራሩ አካል ሊሆን ይችላል።መጠንቀቅ ያለብን ግንባር በተለምዶ የአንድ ቡድን መሰባሰቢያ ሆኖ ለአምባገነንነት በር ሊከፍት እንደሚችል በታሪክ አይተናል። ወያኔም ግንባር ነው(TPLF)፣ኦነግም ግንባር ነው (OLF)፣ሻብያም ግንባር ነው(EPLF)።የሌሎቹም አገራት እንዲሁ ግንባር (FRONT)የጋራ መጠሪያቸው ነው።ግንባር ከሚለው ወጥተን ሕዝባዊ ጦር ቢባል የአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን የሥልጣን መወጣጫ እንዳይሆን ይረዳል።

ሌላው ክፍተትና መታረም ያለበት ጉዳይ በትግሉ ዙሪያ ተጠያቂነት ያለው ሕዝባዊ ድምጽ የሚሆን አንድ ጠንካራ የመረጃና የሚዲያ ተቋም አለመኖሩ ነው።ምንም እንኳን በግል በፌስቡክና በዩቲዩብ ስርጭት የሚንቀሳቀሱ ቢኖሩም ተደራሽነታቸው በጣም ውስን ነው።አንዳንዶቹም የገቢ ምንጭ በመሆን ያለየሌለ ውሸትና እውነቱ የማይታወቅ የወሬ ጋጋታ የሚረጩበት ሆኗል።ለዚህ ችግር በባለሙያተኞች የተቀናጀ፣ሃላፊነት የሚሰማው፣የሕዝብ ድምጽ የሆነ፣የስርዓቱን ልሳኖች የሚቋቋም ብቻም ሳይሆን ዋጋ ቢስ የሚያደርግ የሚዲያ ተቋም ማቋቋም የግድ ይላል።

ሕዝባዊ እምቢተኛነቱ አነጋውያኑን ብቻም ሳይሆን በተፎካካሪነት ሰሌዳ ከስርዓቱ ጋር ሲያሜፍሩ በነበሩት የፖለቲካ ድርጅቶችና የሚድያ ዘርፎች በተለይም ኢዜማ፣አብን፣ኢሳት በመሳሰሉት ተጠቅጥቀው የነበሩ ፖለቲከኞችና ጋዜጠኞች ያሉበትን ድንኳን እዬለቀቁ ከሕዝባዊው ጎራ ለመቀላቀል ዳር ዳር እያሉ መሆናቸውን አይተናል።ከነበሩበት የጥፋት ጎራ መውጣታቸውን ብንደግፍም ለፈጸሙት ክህደትና የጥፋት ተልእኮ ሕዝቡን ፊት ለፊት ይቅርታ መጠዬቅና እራሳቸውን በማገገሚያ ሰፈር ገድበው የንስሃ ጊዜ እንዲወስዱ ለማሳሰብ እንወዳለን።አይተነው ጊዜ የሚል የጮሌዎች ጅዋጅዌ ቦታ የለውም፤ሊኖረውም አይገባም።በተለይም በአማራው ትግል ውስጥ ገብተው እንዲያንቦጫርቁ

ሊፈቀድላቸው አይገባም።እንዲገቡ ቢፈቀድላቸው ትግሉን የማጨናገፍ ወይም የመጥለፍ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው። የስርዓቱን ወይም የኢዜማንና የአብንን ተልእኮ ይዘው ላለመምጣታቸው እርግጠኛ መሆን አይቻልም። ጊዜው ብልሃትን የሚጠይቅ ስለሆነ በዬዋህነት፣ለአብሮነት ሲባል ትግሉን ለአደጋ አጋልጦ ላለመስጠት ጥንቃቄ ማድረግን ይጠይቃል።

የሥርዓቱ ደጋፊና ጠበቃ የሆነችው አሜሪካ የሕዝባዊ ትግሉ እያደገ መምጣት ስላሳሰባት አምባሳደሯን ወደ ኢትዮጵያና ጎረቤት አገሮች ልካለች።ልዩ መልእክተኛው ማይክ ሃመር ከባለስልጣናቱ ጋር የተነጋገሩ ሲሆን ከትግራይ ተገንጣይ ቡድን ከወያኔም ጋር እንደተወያዩ ታውቋል።ከነዚህ ሃይሎች ጋር የሚነጋገሩት ተባብረው አገሪቱን በተለይም ኤርትራን በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ በሚያስችለው ዙሪያ እንጂ የኢትዮጵያን አንድነት በማስጠበቁና የሕዝቡን ጥያቄ በመመለሱ ዙሪያ እንደማይሆን የታወቀ ነው።ገና ከጅምሩ አምባሳደሩ ፋኖንና ኤርትራን የሰላም ጸሮች ሲሉ ወንጅለዋቸዋል።ታዲያ ከዚህ አይነቱ ሰው ምን ሰላም ይወርዳል ተብሎ ይጠበቃል?የኤርትራ ከቻይናና ከሩስያ ጋር መቀራረቧ ለአውሮፓውያን በተለይም ለአሜሪካ እራስ ምታት ሆኖባቸዋል።እንደምንም ብለው የኢሳያስ አፈወርቂን መንግሥት አሶግደው ለእነሱ ታማኝ አገልጋይ የሆነ አገዛዝ ማስፈን ይመርጣሉ፣ ውይይታቸውም ያንኑ ያካተተ ለመሆኑ እማኝ መጥራት አያስፈልግም። በቀጣይ የኢሳያስን ተቃዋሚዎች ከማሰልጠንና ከማስታጠቅ እንደማይመለሱ የታመነ ነው።

በውጭና በአገር ውስጥ ያለው ኢትዮጵያዊ ከምዕራባውያን በኩል ጥሩ ነገር ይመጣል ብሎ በዬመስሪያ ቤቱ ሰልፍ በመውጣት ጊዜውንና ጉልበቱን ከማጥፋት የተጀመረውን ሕዝባዊ ትግል ቢቀላቀል የበለጠ ውጤታማ ይሆናል።የሕዝቡ ድምጽ የሚሰማው ሲደራጅና ሃይል ሲገነባ ብቻ ነው።ደካማና ለማኝ ይናቃል እንጂ አይከበርም።

በዛሬው እለት ወደ ስቱዲዮ ከመግባታችን ከጥቂት ሰዓት በፊት አንድ ዜና ከአገርቤት የሰማን ሲሆን እሱም ከቀናት በፊት የስርዓቱ ፍርድ ቤት ካለምንም የወንጀል ማስረጃ ለዘጠኝ ወራት በእስርቤት ውስጥ ሲያማቅቅ የከረመውን ዘመነ ካሴን መልቀቁን የሚያበስር ነው።በስርዓቱ እንዲታሰርና ከቀናት በፊት እንፈታ የታዘዘው ፍርድ ቤት ከቀናት በፊት እንዲለቀቅ ቢያዝም ፖሊስ አለቅም በማለት ሲግደረደር ቆይቶ በሕዝቡ ያላሰለሰ ትግል በዛሬው እለት ለመልቀቅ ተገዷል።ዘመነ ካሴን ,ተረከበው ፋኖ ወደ ማረፊያው ሆቴል የወሰደው ሲሆን የባሕርዳር ወጣት ከተማዋን የድል ማእከል አድርጓት ውሏል።

ይህ ድል ለቀጣዩ ትግል ምዕራፍ መከፈቻ እንጂ የመጨረሻው አይደለም።የኦነግ መራሹ የኦሮሙማ ስርዓት ተወግዶ የአማራውና የሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ህልውናና እኩልነት እንዲሁም የአገር አንድ,ት እስኪረጋገጥ ድረስ ትግሉ ይቀጥላል።ዘመነም ሆኑ ሌሎቹ መስዋእት የከፈሉት ለዚህ ትልቅ ዓላማ ስለሆነ ሴረኞች ተገደው በሚያሳዩት ማሽብረክ ረክቶ ትጥቅን መፍታት ወይም ትግሉን ማለዘብ አይገባም።ብረትን መቀጥቀጥና መልክ ማስያዝ እንደጋለ ነው።ስርዓቱ እዬተናደ ለመሄዱ ይህ ማስረጃ ሲሆን ጭራሹን እስኪደመሰስ ድረስና ሌሎቹም በእስር ላይ ያሉትን የማስፈታቱ ትግል ሊቀጥል ይገባል። ዶሮን ሲያታልሏት እንዳይሆን በዚህ መለስተኛ ድል መዘናጋት አያስ,ልግም።ይ,ልጥ ሞራልና ሃይልን አሰባስቦ እስከመጨረሻው ድል መጓዝ ይገባል።ቁርጠኝነትና አንድነት ካለ የማያሶግዱት ጸረ ሕዝብ ሃይል አይኖርም።እንደፍላጎታቸውማ ቢሆን ኖሮ ዘመነ ካሴን ገለው ባሶገዱት ነበር።አሁንም ቢሆን ከመለቀቁ ጀርባ ምን እንደታቀደ ስለማይታወቅ በንቃት መከታተልና መከላከል ተገቢ ነው። የባሕርዳር ወጣትም በከተማ የሚያካሂደውን የሰልፍና ተቃሞ ትግል በስፋት መቀጠል ብሎም ከፍ ወዳለ ደረጃ ማሻገር ይጠበቅበታል።የሌሎቹም ከተማዎች ወጣት እጅ ለእጅ ተያይዞ የትግሉን ጎራ ማስፋት ይኖርበታል።የትውልድ አደራውን ሊወጣ ይገባል።የስርዓቱ ተላላኪ የሆኑትን ሆድ አደሮች

የማሶገድ እርምጃ ለቀጣዩ ትግልና ድል ወሳኝ ነው።ፍርሃትና አድር ባይነት ለስርዓቱ ጉልበት ስለሚሆን ከዚያ መራቅ የጀግና ትውልድ መገለጫ ነው።አንድ ዘመነ ብቻ ሳይሆን በሽዎች የሚቆጠሩ ዘመነዎች በዬእስርቤቱ ስላሉ እነሱን ነጻ የማድረጉ ትግል ይቀጥል።

አገር አፍራሾቹን የኦነግና የወያኔ ወራሪ ሃይል ለማሶገድ ሁሉም አገር ወዳድ አርበኛ ይሁን!

የተጀመረው ሕዝባዊ ተቃውሞ ይቀጣጠል!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር!